# ዜና አመዝኤ



## በዚህ እትም ውስጥ


ኤች አይ ቪ/ኤድስን መከላከልን እንደ አንድ መደበኛ የሥራ ዘርፍ ማቀድ ጠቀሜታው . . . መሆኑ ተገለፀ

ገጽ

ለ... ከ254 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል

ገጽ 3

በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ሲጓጓዝ የነበረ የምግብ ዕርዳታ በግለሰቦች መጋዘን ሲራገፍ ተያዘ

ገጽ 4

... ግብ ኘሮግራም ለኢትዮጵያ የሚያደርገውን ድጋፍ እንደሚቀጥል ተገለፀ

ገጽ 5

ድ... ...ትዮጵያ ሰብዓዊ ዕርዳታ እንደሚያደርግ ተለገፀ

... 7



በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 529259
529262
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፧ www.dppc.gov.et



የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፤ ቅፅ 12 ቁጥር 10 ግንቦት 1998


# በመንግሥትና ተባባሪዎቹ የተቀናጀ ጥረት በሶማሌ ክልል የተከሰተው የከፋ ድርቅ ጉዳት ሳያስከትል መከላከል መቻሉ ተገለፀ

በሶማሌ ክልል ዘንድሮ ተከስቶ የነበረው የዝናብ እጥረት ያስከተለው ድርቅ መንግሥትና ተባባሪዎቹ ባደረጉት ጥረትና ቅንጅታዊ አሰራር የከፋ ጉዳት ሳያስከትል በቁጥጥር ስር መዋሉን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ አብዱላሂ ሀሰን ገለጹ፡፡




ርዕሰ መስተዳድሩ አቶ አብዱላሂ ሀሰን ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የሕዝብ ግንኙነት ቡድን ጋር ሰሞኑን ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ እንደገለጹት ካለፈው ጥር ወር 1998 ዓ.ም ጀምሮ በክልሉ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሕዝብ የምግብ እርዳታ እንዲሁም ከ600 ሺህ ሕዝብ በላይ የውሃ አቅርቦት እንደሚያስፈልገው በተደረገው ጥናት መሰረት የፌዴራል መንግሥት በሰጠው አፋጣኝ ምላሽ ድርቁ የከፋ ጉዳት ሳያስከትል መከላከል መቻሉን ገልጸዋል፡፡ በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አስተባባሪነት በክልላዊ መንግስቱ፣ እንዲሁም በጤና ጥበቃ፣ በግብርናና ገጠር ልማት፣ በውኃ ሀብት ልማት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች መካከል የነበረው የቅርብ ክትትልና ቅንጅታዊ አሰራር፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰጠው ያልተቆጠበ ድጋፍ የተጎጂ ወገኖችን ሕይወት በመታደግ ለተገኘው ውጤት ከፍተኛውን ድርሻ እንዳበረከቱም አቶ አብዱላሂ ሀሰን ገልፀዋል፡፡

እንደርዕሰ መስተዳድሩ ገለፃ በፌዴራል መንግሥት፣ በለጋሽ አካላትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ከተሰሩት የአስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ፣ የሰዎችና የእንስሳት ጤና ክብካቤ፣ የውኃና የዘር አቅርቦት መጠነ ሠፊ ሥራዎች በተጨማሪ ክልሉ በራሱ አቅም የድርቁን አደጋ ለመከላከል በወሰደው እርምጃ ወደ 25 ሚሊዮን ብር በሚጠጋ ወጪ የክልሉ ንብረት የሆኑ 20 ቦቴዎችንና ተጨማሪ 30 ቦቴዎችን ተከራይቶ ለውሀ አቅርቦት ሥራ መድቧል፡፡ 70 የሚሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ የውሃ ጉድጓዶችን አስቆፍሯል፡፡ ከድርቁ ጋር በተያያዘ ለሚከሰቱ የሰውና የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ መድሃኒት ግዥም በማካሄድ ችግሩን ለመቋቋም ተችሏል፡፡


ዜና አመዝኤ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው



በሶማሌ ክልል ዘንድሮ ተከስቶ የነበረው የዝናብ እጥረት ያስከተለው ድርቅ መንግሥትና ተባባዎቹ ባደረጉት ጥረትና ቅንጅዊ አሰራር የከፋ ጉዳት ሳያስከትል በቁጥጥር ስርል ውሏል።

የክልሉ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ቢሮ ኃላፊ አቶ አብሽር ሁሴን በበኩላቸው በዚህ ዓመት ተከስቶ የነበረው ድርቅ ከፍተኛ የነበረ መሆኑን አስታውሰው ቀደም ሲል አጋጥም የነበረው የዕርዳታ በተገቢው ፍጥነት ያለመድረስ ችግር በመሻሻሉ ድርቁን መቋቋም እንደተቻለ ተናግረዋል። የተከሰተው ድርቅ በየወሩ 300 ሺህ ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ማጓጓዝን የሚጠይቅ ከመሆኑም ባሻገር ይህንኑ ዕርዳታ የሚያጓጉዙ 1 ሺህ 600 ከባድ ተሽከርካሪዎች ማስፈለጋቸው ፈታኝነቱን እንደሚያሳይ የጠቆሙት አቶ አብሽር የዕርዳታ ማጓጓዝ ሥራውን ለማቀላጠፍና ለመቆጣጠር የትራንስፖርት ኮሚቴ እስከማቋቋም የተሄደበት ቅንጅታዊ አሰራር አመርቂ ውጤት ማስገኘቱን ገልፀዋል።

የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር፣ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር እና የውሃ ሀብት ሚኒስቴር ባለሙያዎችን በማሰማራት፣ መድሀኒቶችንና የዕርዳታ ቁሳቁሶችን በመላክ ያደረጉት ድጋፍ ለዘንድሮው ዓመት የአደጋ መከላከል ሥራ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳበረከተ አቶ አብሽር አስረድተዋል።

የክልሉ አርብቶ አደር ልማት ማስተባበሪያ ዋና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አህመድ ሽዴ በበኩላቸው ድርቁ በተለይም በአፍዴር ሊበንና ጎዴ ዞኖች የከፋ የድርቅ ሁኔታ መከሰቱንና በዚህም ሳቢያ የእንስሳት በሽታና ሞት አስከትሎ የነበረ መሆኑን ገልፀው በተደረገው የመድሀኒት አቅርቦትና ህክምና ጉዳቱን ለመቀነስ መቻሉን እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ እንስሳቱን በሽያጭና በእርድ የማስወገድ **(destocking)** ሥራ በመሰራቱ በአርብቶ አደሩ ላይ የሚደርሰውን ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ለመቀነስ መሞከሩን ተናግረዋል። ከሁሉም በላይ በሰው ህይወት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ የተደረገው ርብርብ ተሳክቶ አሁን ላለንበት ጥሩ ሁኔታ ደርሰናል ብለዋል።

ከድርቁ ጋር ተያይዘው የተከሰቱ የጤና ችግሮችን በተመለከተም የክልሉ ጤና ቢሮ ሥራውን የሚያስተባብር የአስቸኳይ ጊዜ ግብረ ኃይል ከማቋቋሙም በላይ በድርቁ በከፍተኛ ሁኔታ ከተጎዱት ከ24 ወረዳዎች ውስጥ ወደ 16 ተንቀሳቃሽ የጤና ቡድኖችን በማሰማራት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባደረገው የባለሙያና የቁሳቁስ ድጋፍ ችግሩን ለመከላከል መቻሉን የጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ ዶክተር አብዱልአዚዝ ኢብራሂም ገልፀዋል።

## ኤች አይ ቪ/ኤድስን መከላከልን እንደ አንድ መደበኛ የሥራ ዘርፍ ማቀድ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ ተገለፀ

በአሁኑ ጊዜ በብሔራዊ ብሎም በአለም አቀፋፍ ደረጃ በሰው ልጆች ላይ ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ያስከተለውንና የወቅቱ ዋነኛ ችግር የሆነውን የኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሽታን የመከላከል ሥራን በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ እንደ አንድ መደበኛ የሥራ ዘርፍ በማቀድ ለተግባራዊነቱ ሁሉንም ሠራተኛ ማንቀሳቀሱ ጠቀሚታው ከፍተኛ መሆኑን የአመዝኤ ዋና ዳይሬክተር ገለፁ።

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ ግንቦት 25 ቀን 1998 ዓ.ም በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ መከላከልና ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ከፌዴራል የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር የግማሽ ቀን ባዘጋጀው የግንዛቤ ማጎልበቻ ትምህርታዊ ኘሮግራም ላይ እንዳስታወቁት ኤድስ የእያንዳንዱን ቤት ያንኳኳና የሁሉም ጉዳይ መሆኑ ይኸን ችግር



በዚሁ ጊዜ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ እያስከተለ ያለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች በጋራ ለመዋጋት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አመራሮችና ሠራተኞች እያከናወኑት ያለው ተግባር የሚያበረታታ መሆኑ ተገለጸ፡፡

መዋጋት ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ኃላፊነት ሆኗል ብለዋል፡፡ በመሆኑም በሽታውን የመከላከሉ ሥራ ከቤታችን ቢጀምርም በያለንበት ከመደበኛ ሥራችን ጋር በማካተት በዕቅድና በተደራጀ መልኩ ማከናወኑ ደግሞ ለስኬታማነቱ ይበልጥ የሚረዳን ይሆናል ሲሉ ዋና ዳይሬክተሩ አክለው ገልፀዋል፡፡ በዚህ ረገድ በሠራተኛው በራሱ ምርጫ በኤጀንሲው በተቋቋመው የኤች አይ ቪ/ኤድስ ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ጎን በመሰለፍ ከደመወዙ በመቶኛ በማዋጣት ያቋቋመው የኤድስ ፈንድ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ የኤጀንሲው ሠራተኞች ካሉ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል አቅም መፍጠሩን አመልክተው ኤጀንሲውም በማናቸውም ወቅት አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል፡፡

በዚሁ ትምህርታዊ ኘሮግራም ላይ ከ500 በላይ ለሚሆኑ የኤጀንሲው ሠራተኞች ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በመከላከል ረገድ ያላቸውን ግንዛቤ ለማዳበር እንዲረዳ የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርት ለመስጠት ከፌዴራል የኤች አይቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት የመጡ ባለሙያዎች ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በአሁኑ ጊዜ በብሔራዊና አለም አቀፍ ደረጃ የሚገኝበት ሁኔታ እና በሽታውን ለመከላከል በመንግሥት እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች በሚሉ ርዕሶች ሰፋ ያለ ትምህርታዊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

በዚሁ ጊዜ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ እያስከተለ ያለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች በጋራ ለመዋጋት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አመራሮችና ሠራተኞች እያከናወኑት ያለው ተግባር የሚያበረታታ



መሆኑን የገለጹት ባለሙያዎቹ ችግሩን ለመቅረፍ መንግሥት ፖሊሲ ቀርጾና የአጭርና ረጅም ጊዜ ዕቅዶች አውጥቶ እየሰራ ባለበት ወቅት ሁሉም በየተሰማራበት የሥራ መስክ እንዲህ በተደራጀ መልኩ ችግሩን ለመዋጋት መነሳሳተት እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

በዚሁ ኘሮግራም ላይ ተሳታፊ የሆነው መላው የኤጀንሲው ሠራተኛ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን አስመልክቶ ሰፊ ውይይት ያደረገ ከመሆኑም በላይ ሠራተኞቹ ላነሷቸው ተያያዥ ጥያቄዎች በባለሙያዎቹ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## ለግንቦት ወር ከ254 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል

በተለያዩ ክልሎች የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ለግንቦት ወር 1998 ዓ.ም የሚሆን ቀለብ በጠቅላላው 254 ሺህ 468.9 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል፡፡

ከዚሁ ለወሩ ከተመደበው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 174 ሺህ 485 ኩንታል በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ቀሪው 79 ሺህ 983.9 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተመደበ መሆኑን

በተለያዩ ክልሎች የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ለግንቦት ወር 1998 ዓ.ም የሚሆን ቀለብ በጠቅላላው 254 ሺህ 468.9 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል::

ከኤጀንሲው የዕርዳታ ፕሮግራሞች አፈጻጸምና ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

ለየክልሎች የሚመደበው የምግብ ዕርዳታም በየክልሉ እንደሚገኘው ችግር ስፋትና ጥልቀት የሚለያይ ሆኖ በዚሁ መሠረት ለግንቦት ወር ከተመደበው 254 ሺህ 468.9 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለኦሮሚያ 132 ሺህ 722.4 ኩንታል፣ ለሱማሌ 67 ሺህ 392 ኩንታል፣ ለአማራ 26 ሺህ 300 ኩንታል፣ ለአፋር 8 ሺህ 284.5 ኩንታል፣ ለጋምቤላ 7 ሺህ 530 ኩንታል፣ ለደቡብ ህዝቦች 7 ሺህ 266 ኩንታል እና ለድሬደዋ 4 ሺህ 674 ኩንታል መመደቡን ለማወቅ ተችሏል::

## በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ሲጓጓዝ የነበረ የምግብ ዕርዳታ በግለሰቦች መጋዘን ሲራገፍ ተያዘ

ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ማዕከላዊ መጋዘናት ተጭኖ በድርቅ ለተጎዱና ለሴፍቲኔት ተጠቃሚ ወገኖች ሲጓጓዝ የነበረ 594 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ በተለያዩ ከተሞች በግለሰቦች መጋዘን ከተራገፈ በኋላ እና ሲራገፍ በህብረተሰቡ ጥቆማ እጅ ከፍንጅ ሊያዝ ችሏል::



በግለሰብ መጋዘን ተራግፎ የተያዘ የዕርዳታ እህል

ከዚሁ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 452 ኩንታል ስንዴ እና 10 ኩንታል የምግብ ዘይት በድምሩ 462 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ናዝሬት ከሚገኘው የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ማዕከላዊ መጋዘን ተጭኖ ሱማሌ ክልል አፍዴር ዞን ሀርጌሌና ባሬ ወረዳዎች ለሚገኙ ተረጂ ወገኖች ሲጓጓዝ አዋሳና ነገሌ ከተሞች ላይ በግለሰቦች መጋዘን ውስጥ ከተራገፈ በኋላና በመራገፍ ላይ እንዳለ በህብረተሰቡ ጥቆማ ሊያዝ ችሏል:: ቀሪው 97 ኩንታል ስንዴና 22 ኩንታል ምስር እና 3 ኩንታል ዘይት ደግሞ ኮምበልቻ ከሚገኘው የኤጀንሲው ማዕከላዊ መጋዘን ተጭኖ አማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ሲሪንቃ ለሚገኙ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ሲጓጓዝ ሲሪንቃ ላይ በግለሰብ መጋዘን ከተራገፈ በኋላ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ውሏል::

ወደ ሱማሌ ክልል ተመድቦ ሲጓጓዝ ከነበረው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 390 ኩንታል ስንዴና 10 ኩንታል የምግብ ዘይት ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም ከናዝሬት ማዕከላዊ መጋዘን ጭኖ ሀርገሌ ወረዳ ሀይሬ ማከፋፈያ ጣቢያ ለማድረስ ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ጋር ውል በገባው አንድ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከካሪዎች ባለንብረቶች ማህበር ስም ከተመዘገበና ዕርዳታው ሲጓጓዝበት ከነበረው የሠሌዳ ቁጥሩ ኢት ኮድ 3 - 00074 የሆነ የጭነት ተሽከርካሪ ላይ በአዋሳ ከተማ ከምሽቱ 5 ሰዓት ተኩል ላይ በግለሰብ መጋዘን ውስጥ ሲራገፍ የአካባቢው ህብረተሰብ ለፖሊስ ባደረገው ጥቆማ እጅ ከፍንጅ ሊያዝ ችሏል:: የአዋሳ ከተማ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቴክኒክ ክፍል ክፍል ሀላፊ ም/ሳጅን ገነት ኤርባሞ ለአመዝኤ የህዝብ ግንኙት ባልደረቦች እንደገለጹት የዕርዳታ እህሉ አንድ የግለሰብ መጋዘን ውስጥ በመራገፍ ላይ ሳለ በህብረተሰቡ ጥቆማ እጅ ከፍንጅ በተያዘበት ወቅት ተሽከርካሪው ከጫነው 400 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 140 ኩንታል ወይም 280 ከረጢት ስንዴ በግለሰቡ መጋዘን ገብቶ እንደነበር ገልፀዋል:: አያይዘውም አስፈላጊው ማስረጃ ከተሰባሰበ በኋላ የተራገፈው እህል ወደ ተሽከርካሪው ላይ ተመልሶ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር እንዲቆይ መደረጉን አብራርተዋል:: ጉዳዩን አጣርቶ ይህን ኃላፊነት የጎደለው ህገወጥ ድርጊት ፈጻሚዎች ለፍርድ ለማቅረብ ማስረጃዎች እየተጠናቀሩ መሆኑን የወንጀል ምርመራ ክፍል ኃላፊዋ አክለው ገልፀዋል::

በተመሳሳይ ሁኔታም ከናዝሬት ማዕከላዊ መጋዘን ተጭኖ ሱማሌ ክልል እፍዴር ዞን

ባሬ ወረዳ ለሚገኙ ተረጂዎች ሲጓጓዝ የነበረ 62 ኩንታል ስንዴ ሚያዝያ 27 ቀን 1998 ዓ.ም ነገሌ ላይ በግለሰብ መጋዘን ውስጥ ተራግፎ መገኘቱንና እህሉ ለብልሽት እንዳይዳረግና በወቅቱ ለተጎጂ ወገኖች እንዲደርስ ወደ ማከፋፈያ ጣቢያው በግለሰቦች መጋዘን በማከማቸት ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉ ወገኖች እየተበራከቱ መጥተዋል። በመሆኑም ይሄንን ሁኔታ ለመቆጣጠርና ብሎም የድርቅ ተጎጂ ወገኖችን ሕይወት ለመታደግ የሚላክ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ እህል ለታሰበለት



እንዲጓጓዝ መደረጉንና ጉዳዩ በምርመራ ላይ የሚገኝ መሆኑን የነገሌ ከተማ ልዩ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት አስታውቋል። በጽ/ቤቱ የወንጀል መከላከል ክፍል ኃላፊ ም/ኢንስፔክተር ኤደን ዱባ ጉዮ በሥፍራው ለተገኙት የአመዝኤ ሕዝብ ግንኙነት ባልደረቦች እንደገለጹት የዕርዳታ እህል ከታሰበለት ዓላማ ውጭ በተለያዩ ሁኔታዎች በተለይም በነገሌ ከተማ ዓላማ ብቻ እንዲውል በማስቻል ረገድ ኃላፊነቱ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ብቻ ሳይሆን በየደረጃው ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች እንዲሁም የክልል የፖሊስ አካላትና የህብረተሰቡም ጭምር በመሆኑ እያንዳንዱ ወገን ሁኔታውን በንቃት በመከታተል የተቀናጀና ጠንከር ያለ የክትትልና የቁጥጥር እርምጃ መውሰድ እንደሚገባ አመልክተዋል።

> ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ጋር ውል በገባው አንድ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ባለንብረቶች ማህበር ስም ከተመዘገበና ዕርዳታው ሲጓጓዝበት ከነበረው የሡሌዳ ቁጥሩ ኢት ኮድ 3 -00074 የሆነ የጭነት ተሽከርካሪ ላይ በአዋሳ ከተማ ከምሽቱ 5 ሰዓት ተኩል ላይ በግለሰብ መጋዘን ውስጥ ሲራገፍ በአካባቢው ህብረተሰብ ለፖሊስ ባደረገው ጥቆማ እጅ ከፍንጅ ሊያዝ ችሏል።

## የዓለም ምግብ ኘሮግራም ለኢትዮጵያ የሚያደርገውን ድጋፍ እንደሚቀጥል ተገለፀ

የዓለም ምግብ ኘሮግራም በኢትዮጵያ የተከሰተውን የድርቅ አደጋ ለመቋቋም በሚደረገው እንቅስቃሴ በእስከአሁኑ ካደረገው ድጋፍ ባሻገር በቀጣይም ለጋሾችን በማስተባበር አስፈላጊው እገዛ እንዲገኝ የተቻለውን ሁሉ እንደሚያደርግ አንድ የድርጅቱ ከፍተኛ ኃላፊ ገለፁ።

ሚስተር ሚካኤል ቢ ስታይተን የዓለም ምግብ ኘሮግራም ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ዳይሬክተር በኢትዮጵያ በሚካሄደው የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ አቅርቦት ዙሪያ ከአቶ ሲሞን መቻል የአደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ጋር ግንቦት 7 ቀን 1998 ዓ.ም. በተወያዩበት ወቅት እንደገለጹት ድርጅቱ ሀገሪቱ የድርቁን አደጋ ለመቋቋም እያደረገች ላለው የተቀናጀ ጥረት በእስካሁኑ ከሰጠው ድጋፍ ባሻገር ተጨማሪ ዕገዛና ዕርዳታ እንዲገኝ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል።

ሚስተር ማይክል በዚሁ ጊዜ እንደተናገሩት የጉብኝታቸው ዋነኛ ዓላማ በያዝነው ዓመት የተከሰተውን ችግር ለመቋቋም የኢትዮጵያ መንግሥት ከዓለም ምግብ ኘሮግራም ጋር ባካሄደው የተቀናጀ እንቅስቃሴ የተመዘገቡ ውጤቶችን፣ ያጋጠሙ ችግሮችንና በቀጣይም ሊጤኑ በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት መሆኑን አመልክተዋል። አያይዘውም በእስካሁን ችግሩን ለመቋቋም በተደረገው እንቅስቃሴ ውጤት ቢመዘገብም የዕርዳታ

እህል በማጓጓዝ በኩል የታየው ችግር በዘላቂነት ለመፍታትና የአስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ አቅርቦትን ለማቀላጠፍ እንዲቻል የዓለም ምግብ ኘሮግራም አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል፡፡

አቶ ሲሞን መቻለ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይ ክተር በበኩላቸው በዚሁ ጊዜ እንደገለጹት በሀገራችን የዓለም ምግብ ኘሮግራም በሰብዓዊ ዕርዳታ በረጅም ዘመን አጋርነቱ ቁልፍ ሚና መጫወቱን አብራርተዋል፡፡

በቁጥጥር ሥር መዋሉንና ከመጋቢት ወር አጋማሽ ወዲህ በሱማሌ ክልል በጣለው ዝናብ ሁኔታው መሻሻሉን ያመለከቱት ዋና ዳይሬክተር ሆኖም በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎች ሁኔታዎች የቅርብ ክትትል እንደሚደረግባቸውና በመጪው በሰኔ ወርም መደበኛ ጥናት የሚያደርጉ አጥኚ ቡድኖች በልግ አብቃይና በአርብቶ አደር አካባቢዎች እንደሚሰማሩ አብራርተዋል፡፡ በዚያን ወቅት በሚደረግ ጥናት መነሻነትም ከሰኔ ወር በኋላ የሚኖረው የዕርዳታ ፍላጎት ተገቢው እርምጃ እንደሚወስድ ጠቁመዋል፡፡

በእስካሁን ችግሩን ለመቋቋም በተደረገው እንቅስቃሴ ውጤት ቢመዘገብም የዕርዳታ እህል በማጓጓዝ በኩል የታየው ችግር በዘላቂነት ለመፍታትና የአስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ አቅርቦትን ለማቀላጠፍ እንዲቻል የዓለም ምግብ ኘሮግራም አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡



አያይዘውም በያዝነው ዓመት በታህሳስ በተደረገው ጥናት በአገሪቱ የአስቸኳይ ዕርዳታ እንደሚያስፈልገው ከተያዘው 2.6 ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ 70 በመቶ የሚሆነው ተረጅ በአርብቶ አደሮች አካባቢ እንደሚገኝ አመልክተው፣ በአደጋ የተጎዳውን የህብረተሰብ ክፍል ለመደገፍ ከቀረበው 340 ሺህ ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 70 በመቶ መገኘቱን አብራርተዋል፡፡

ምግብ ነክ ባልሆኑ ዕርዳታዎች በኩል ያለው የዕርዳታ ምላሽ የተፈለገውን ያህል እንዳልሆነና ከተጠየቀው ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች ውስጥ 20 በመቶ ብቻ እንደተገኘ ያመለከቱት ዋና ዳይሬክተሩ እንደምግብ ዕርዳታው ሁሉ ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች ግዜትም ወሳኝ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ችግሩ በአሁኑ ጊዜ በመንግሥትና በተባባሪዎቹ የተቀናጀ እንቅስቃሴ

በሱማሌ ክልል የተከሰተው የትራንስፖርት ችግር በአስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ አቅርቦት ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን በስፋት ያብራሩት ዋና ዳይሬክተሩ በብሔራዊ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴ አመራር ሰጭነት፣ የብሔራዊ ትራንስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ የግሉን የትራንስፖርት ዘርፍ፣ ከማስተባበር በተጓዳኝ የዕለት ዕርዳታ ለማጓጓዝ በተቋቋመው የዕለት ደራሽ ዕርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት አማካይነት በማጓጓዝና በመከላከያ ሠራዊት አማካይነት ተሽከርካሪዎችን በማጀብ በተቻለ አቅም ችግሩን ለመቋቋም ጥረት ተደርጓል ብለዋል፡፡ ይሁንና የግሉ ትራንስፖርት በማይገባባtው ቦታዎች የዕለት ደራሽ ዕርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት አገልግሎት በመስጠት የላቀ አስተዋጽዖ እያበረከተ ቢገኝም ተሽከርካሪዎች ረጅም ጊዜ በማገልገላቸው ችግሩን ለመፍታት ለሚደረገው ጥረት ስኬታማነት በዓለም ምግብ ኘሮግራም ድጋፍ ያሻል ብለዋል፡፡

# ድርጅቱ ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ ዕርዳታ እንደሚያደርግ ገለፀ

> በአሁኑ ጊዜ የጉብኝታቸው ዋና ዓላማ በአፍሪካ ቀንድ የተከሰተውን ድርቅ ለመመልከትና በቀጣይ በእስላሚክ ኮንፈረንስ ድርጅት በኩል ስለሚወሰደው እርምጃ ለድርጅቱ ዋና ፀሐፊ አስፈላጊውን መረጃ ለማቅረብ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የእስላሚክ ኮንፍረንስ ድርጅት (Organization of the Islamic Conference) **(OIC)** በኢትዮጵያ የተከሰተውን የድርቅ አደጋ ለመከላከልና ለመቋቋም ለሚደረገው እንቅስቃሴ ሰብዓዊ ዕርዳታ ለመስጠት ጥረት እንደሚያደርግ አምባሳደር ሰይድ ቢን ካሊፋ መሪና የኳታር ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክተር የተመራው ከፍተኛ ልዑካን ቡድን ገለፀ፡፡ በአምባሳደር ሰይድ ቢን ካሊፋ የተመራው ከፍተኛ ልዑካን ቡድን ይህን የገለፀው በኢትዮጵያ የተከሰተውን የድርቅ አደጋ ለመከላከልና ለመቋቋም ስለተወሰደውና በመወሰድ ላይ ስላለው እርምጃ ከአቶ ገብረመድህን በላይ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ጋር ግንቦት 10 ቀን 1998 ዓ.ም. ውይይት ባደረጉበት ወቅት ነው፡፡

የዚሁ 57 የአረብ፣ የአፍሪካና የኢስያ ሀገሮች አባል የሆኑበት ድርጅት ከፍተኛ ልዑካን ቡድን አባላት በውይይቱ ወቅት በየበኩላቸው እንደተናገሩት በአሁኑ ጊዜ የጉብኝታቸው ዋና ዓላማ በአፍሪካ ቀንድ የተከሰተውን ድርቅ ለመመልከትና በቀጣይ በእስላሚክ ኮንፈረንስ ድርጅት በኩል ስለሚወሰደው እርምጃ ለድርጅቱ ዋና ፀሐፊ አስፈላጊውን መረጃ ለማቅረብ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በኢትዮጵያ የሚያደርጉት ጉብኝትም የዚሁ አካል መሆኑን ጠቁመው፣ በሱማሌ ክልል የተከሰተውን ድርቅ በቦታው ተገኝቶ በመመልከትና በኢትዮጵያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስለችግሩ በመወያየት ከሚያገኙት ግንዛቤና እውነታ በመነሳት ድርጅቱ አስፈላጊውን ሰብዓዊ ዕርዳታ እንደሚያበረክት ያላቸውን እምነት ገልፀዋል፡፡ ለዚሁም የበኩላቸውን ጥረት እንደሚያደርጉ አመልክተዋል፡፡
አያይዘውም በኢትዮጵያ በአጠቃላይም በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ለተከሰተው አስከፊ የድርቅ አደጋ ድጋፍ ለመስጠት እንዲቻልም የእስላሚክ ኮንፈረንስ ድርጅት ዋና ፀሐፊ በድርጅቱ ስም ለአባል ሀገራት የዕርዳታ ጥያቄ ማቅረባቸውንና ከሀገሮቹም በጎ አዝማሚያ መታየቱንም ጠቁመዋል፡፡ አቶ ገብረመድህን በላይ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር በበኩላቸው በዚሁ ጊዜ እንደተናገሩት በያዝነው ዓመት በአገሪቱ የአስቸኳይ ዕርዳታ ከሚፈልገው 2.6 ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ ወደ 1.7 ሚሊዮን የሚጠጋው በአገሪቱ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ በሚገኘው የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢ ነው፡፡ የዕርዳታ ፍላጎቱ በምግብና ምግብ ነክ ባልሆኑ ዕርዳታዎች ላይ አትኩሮ አስፈላጊው ዕርዳታ ለተረጂዎች በመቅረብ ላይ እንደሚገኝ ለልዑካን ቡድኑ አስረድተዋል፡፡

አያይዘውም ይህንኑ ተረጂ ህዝብ በመደገፍ በምግብ ረገድ ግምቱ 145 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሆነ 3.4 ሚሊዮን ኩንታል የዕርዳታ እህል የዕርዳታ እንቅስቃሴ ከተጀመረበት ከጥር ወር 1998 ዓ.ም ጀምሮ እንደሚያስፈልግ ገልፀው፣ ከዚህ ውስጥ ከ2.3 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ተገቃቷል ብለዋል፡፡ ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች የውሃ፣የጤና፣ የግብርና አቅርቦቶችን እንደሚያካትት የገለጹት ም/ዋና ዳይሬክተሩ በዚህ ረገድ ከሚያስፈልገው 111.1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ውስጥ የተገኘው ከ20 በመቶ እንደማይበልጥ አመልክተው፣ ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች ድጋፍ እንደሚያሻ አብራርተዋል፡፡

የእስላሚክ ኮንፍረንስ ድርጅት ከፍተኛ የልዑካን ቡድን አባላት ለሀገራችን ጉዳይ ትኩረት በመስጠት ላደረጉት ጉብኝት ምስጋናቸውን ያቀረቡት ምክትል ዋና ዳይ ክተር ይህም ከኳታርና ከድርጅቱ አባል ሀገሮች ጋር ያለውን የቆየ ግንኙነት ያመለክታል ብለዋል፡፡፡